DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS

# በት/ቤት ሰራተኞች በተማሪ ላይ የሚደርስን ወሲባዊ በደል መከላከያ ፖሊሲ

## I. አላማ እና ስፋት

የዲሲ የህዝብ ት/ቤቶች (DCPS) እያንዳንዱ ተማሪ የመወደድ፤ የመፈተን ስሜት እና ማህበረሰብን በአወንታዊ ሁኔታ እንዲለውጥ እና በህይወት ውስጥም ዕድገት ላማሰየት መዘጋጀቱን ለማረጋገጥ በቁርጠኝነት ይሰራል። በዲሲፒኤስ (DCPS) ሁሉንም ልጅ ጠንካራ፤ አስደሳች እና አካታች የሆነ ትምህርታዊ፤ ማህበረሰባዊ እና ስሜታዊ ተሞክሮ በመስጠት ሁሉም ተማሪዎች ለኮሌጅ እና ለስራ ብቁ የሆኑ መሆኑን ለማረጋገጥ በቁርጠኝነት ለመስራት ተነስተናል። እንደዚሁ ቁርጠኝነት አንድ አካል፤ ዲሲፒኢኤስ (DCPS) ሁሉንም ልጅ የሚረዳ እና እያንዳንዱ ተማሪ አስደሳች እና ጠንካራ የሆነ የትምህርት ተሞክሮ ያለው መሆኑን እርግጠኛ ለመሆን ምቹ እና አስተማማኝ የመማር ሁኔታ ለመፍጠር ይሰራል።

ይህ ፖሊሲ የ 2018ቱን የት/ቤት ደህንነት ማሻሻያ ህግ (School Safety Omnibus Amendment Act of 2018 (“School Safety Act”).[1] ጨምሮ ተግባራዊ በሚሆን ህግ ላይ እንደተደነገገው በት/ቤት ሰራተኞች በተማሪ ላይ የሚደርስን ወሲባዊ በደል መከላከልን በሚመለከት የዲሲፒኤስን (DCPS) መስፈርቶች ያመለክታል። የት/ቤት ሰራተኛ (staff) የሚለው ቃል በት/ቤት ደህንነት ህግ በጥቅሉ እንደሚተረጉመው  የት/ቤት ተቀጣሪን ወይም ፍቃደኛ ሰራተኛ፤ ት/ቤቱ ኮንትራት የሚዋዋለው አካል ሰራተኛ፤ ወይም ት/ቤቱ የስምምነት ውል ወይም የመግባቢያ ውል (Memorandum of Agreement or a Memorandum of Understanding) በማድረግ ት/ቤቱ አብሮ የሚሰራው አካል ተቀጣሪ ወይም የበጎ ፈቃድ ሰራተኛ እንዲሁም የት/ቤቱ ወይም በትምህርት ቤቱ ድጋፍ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ተወካይ ሆኖ የሚሰራ ማለት ነው።

## II. ሥልጣን እና ተፈጻሚነት ያለው ህግ

| **ምንጭ** | **ጥቅስ (Citation)** |
|---|---|
| የፌዴራል ህግ | የ2015 ቱ ሁሉም ተማሪ ከግብ ይደርሳል ህግ (Every Student Succeeds Act of 2015, 129 Stat. 2120, 20 U.S.C. § 7926) |
| | የ1972 የትምህርት ማሻሻያ ህግ ርዕስ IX (Title IX of the Education Amendments Act of 1972 (Title IX), 20 U.S.C. §1681 *et seq.*) |
| ዲሲ ህግ<br>(DC Law) | የ 2018ቱ የት/ቤት ደህንነት ማሻሻያ ህግ (School Safety Omnibus Amendment Act of 2018) (ዲሲ ህግ 22-294 ፤ ዲሲ ህግ (D.C. Code ) ቁጥር 38-951.01፤ et seq.) |
| | የ1994 ፀረ-ወሲባዊ በደል ህግ  (ዲሲ ህግ 10-257; ዲሲ ህግ ቁጥር 22-3001, et seq.) |
| | የግድ ማሳወቅ መስፈርቶች (ዲሲ ህግ ቁጥር 4-1321.02) |
| | ዲሲ ኦፊሺያል ህግ ቁጥር 4-1501 et seq.) (ለህጻናት ለሚሰጡ የመንግስት አገልግሎቶች የወንጀል ምርመራ) |
| | የ1977 ዲሲ ሰብዓዊ መብቶች ህግ ፤ዲሲ ህግ ቁጥር 2-1401 *et seq.* |
| ዲሲ ሥርዓቶች | 6-B DCMR ቁጥር 400 et seq. (የመንግስት ሰራተኝነት የብቁነት መስፈርቶች) |

## III. ትርጉሞች

[1] ዲሲ ህግ ቁጥር 38-951.01, et seq.

**የልጆች ጥቃት (Child abuse)** ማለት፤

(ሀ) ልጆች ላይ አካላዊም ሆነ የአእምሮ ጉዳት ማድረስ፤
(ለ) **ወሲባዊ ጥቃት** ፤ ከዚህ በታች እንደሚተረጎመው ማለት ነው፤ ወይም ልጆችን መበዝበዝ፤ ወይም
(ሐ) ልጆችን በግድየለሽነት ወይም አግባብነት በሌለው ሁኔታ መያዝ። (ዲሲ ህግ፤ ቁጥር 38-951.01(1))
**ለአቅመ አዳም ያልደረሰ (Minor)** ማለት ገና 18 ዓመት ያልደረሰ ሰው ማለት ነው (ዲሲ ህግ፤ ቁጥር 22-3001 (5A))

**ወሲባዊ ጥቃት** ማለት፤ በ1994ቱ ወሲባዊ ጥቃትን የመከላከል ህግ (ዲሲ ህግ 10-257፤ ዲሲ ህግ 3020.51(4))፤ የሚከተሉትን ህጎች የሚጥስ ማንኛውም ዓይነት ድርጊት እንደሆነ ተደርጎ ይቆጠራል፤

(ሀ) የዲሲ ህግ 22-1834 (ልጆችን ለወሲብ ዓላማ ማዘዋወር)፤

(ለ )ዲሲ ህግ፤ ቁጥር 22-2704 (ለዝሙት አዳሪነት ዓላማ ልጅን ከቤቱ ወይም ከቤቷ እስገድዶ ወይም ገፋፍቶ መውሰድ፤ እንዲህ ዓይነቱን ልጅ ማገት)፤

(ሐ) ዲሲ ህግ፤ ቁጥር 22-3001, et seq. (ወሲባዊ በደል)፤ በዚህ ሳይመሰን የሚከተሉትን ጨምሮ፤ የልጅ ወሲባዊ በደል፤ ለአቅመ አዳም ያልደረሰ ልጅ ወሲባዊ በደል፤ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ወሲባዊ በደል፤ ልጅን ወይም ለአቅመ አዳም ያልደረሰን ልጅ ማነሳሳት፤ ወይም እውን ወይም ልብ-ወለድ ከሆነ ህጻን ጋር ወሲባዊ ንክኪ ለማድረግ ማመቻቸት፤ ወይም

(መ) ዲሲ ህግ፤ ቁጥር 22-3102 (ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆችን በመጠቀም ወሲባዊ ድርጊት)።[2]

**አግባብነት የሌለው ወሲባዊ ስነ-ምግባር** ማለት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጨምሮ ማንኛውም የቃልም ሆነ የቃል ያልሆነ፤ የጽሁፍ ወይም የኤሌክትሮኒክ ግንኙነት፤ ወይም ሌላ ማንኛውም ወደ ልጁ ወይም ከልጁ ጋር ወሲባዊ ግንኙነት ለማድረግ የታቀደ ድርጊት ማለት ነው።

ሀ ለወሲብ መጋበዝ፤
(ለ) ለፍቅር ጓደኝነት ለመገናኘት መለማመጥ፤
(ሐ) ወሲብ-ነክ ውይይት ውስጥ ማሳተፍ፤
(መ) የወሲብ ስሜት ቀስቃሽ የሆኑ አስተያየቶችን መስጠት፤
(ሠ) ከዚህ በፊት ያጋጠሙ ወሲብ-ነክ ችግሮችን ማብራራት፤ ወይም
(ረ) ወሲብ-ነክ የሆኑ የተፈጥሮ አካላትን ማሳየት (ዲሲ ህግ፤ ቁጥር 38-951.01(4))

**የት/ቤት ሰራተኛ (Staff)** ማለት የት/ቤት ተቀጣሪን ወይም ፍቃደኛ ሰራተኛ፤ ት/ቤቱ ኮንትራት የሚዋዋለው አካል ሰራተኛ፤ ወይም ት/ቤቱ የስምምነት ውል ወይም የመግባቢያ ውል (Memorandum of Agreement or a Memorandum of Understanding) በማድረግ ት/ቤቱ አብሮ የሚሰራው አካል ተቀጣሪ ወይም የበጎ ፈቃድ ሰራተኛ እንዲሁም የት/ቤቱ ወይም በትምህርት ቤቱ ድጋፍ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ተወካይ ሆኖ የሚሰራ ማለት ነው። (*የዲሲ ህግ፤ ቁጥር 38-951.01(5))* ን ይመልከቱ።

[2] በዚህ ትርጓሜ ላይ ስለቀረቡት ከሁሉም አካባቢያዊ ህጎች የተወሰዱ አንቀጾችን በሚመለከት እባክዎ አባሪ ሀ ን ይመልከቱ።

**የተማሪ ወሲባዊ ጥቃት** ማለት ከላይ እንደተተረጎመው እና በ 1994ቱ ጸረ-ወሲባዊ ጥቃት ህግ (ዲሲ ህግ፤ 10-257; ዲሲ ህግ 3020.51(4))) እንደተተረጎመው በትምህርት ቤት ተማሪ ላይ የተፈጸመ **ወሲባዊ ጥቃት** ማለት ነው። (ዲሲ ህግ፤ ቁጥር 38-951.01(6))

## IV. መስፈርቶች

### (ሀ) የሰራተኛ ስልጠና እና የስነ-ምግባር መስፈርቶች

1. የሰራተኛ ስልጠና መስፈርቶች

የዲሲፒኢኤስ (DCPS) ማዕከላዊ ቢሮ የሚከተሉትን መመሪያዎች ያካተተ በጽታዊ ስነ-ምግባር፤ የተማሪ ወሲባዊ ጥቃት እና የልጅ ጥቃት ላይ አስፈላጊውን ስልጠና የመስጠት ሃላፊነት ያለው ነው፤

(ሀ) አላስፈላጊ ወሲባዊ ባህሪያትን፤ የተማሪ ወሲባዊ ጥቃትን እና የልጅ ጥቃትን ማወቅ እና ሪፖርት ማድረግ፤
(ለ) አላስፈላጊ ወሲባዊ ባህሪያትን፤ የተማሪ ወሲባዊ ጥቃትን እና የልጅ ጥቃት ታሪኮችን ድጋፍ በሚሰጥ፤ ተገቢ በሆነ እና አስከፊነቱን ባገናዘበ መልኩ መቀበል
(ሐ) አላስፈላጊ ወሲባዊ ባህሪያትን፤ የተማሪ ወሲባዊ ጥቃትን እና የልጅ ጥቃትን ጠቋሚ የሆኑ ምልክቶችን እና ተጽእኖዎችን መከላከል፤
(መ) አላስፈላጊ ወሲባዊ ባህሪያትን፤ የተማሪ ወሲባዊ ጥቃትን እና የልጅ ጥቃትን ሪፖርት ማድረግን በሚመለከት ከተማሪዎች እና ወላጆች ጋር መገናኘት፤ እና
(ሠ) ሌሎች በት/ቤቱ ማህበረሰብ የሚለዩ ተገቢ ርዕሶችን።

ከ 2020-21 የትምህርት ዓመት የመጀመሪያው ቀን ጀምሮ ሁሉም ሠራተኞች አላስፈላጊን ወሲባዊ ባህሪያትን፤ የተማሪ ወሲባዊ ጥቃትን እና የልጅ ጥቃት የመከላከል፤ የማወቅ እና ሪፖርት የማድረግ ሥልጠና ማጠናቀቅ አለባቸው። በመሆኑም ይህ አስፈላጊ ስልጠና ለአዲስ ተቀጣሪዎችም መሟላት ያለበት ሲሆን ለሁሉም ሰራተኞች ቢያንስ በየሁለት ዓመቱ መሰጠት አለበት። ይህ አስፈላጊ ስልጠና መሟላት እና አለመሟላቱ በዲሲፒኤስ (DCPS) የሰራተኛ አገልግሎቶች ቢሮ ክትትል ይደረጋል። የእያንዳንዱ የዲሲፒኤስ (DCPS) ት/ቤት ዳይሬክተር ከሰራተኛ አገልግሎቶች ቢሮ ጋር በመቀናጀት ሁሉም የት/ቤቱ ሰራተኞች መስፈርቱን ማሟላታቸውን ያረጋግጣል።

2. የሰራተኛ የህይወት ታሪክ ምርመራ መስፈርቶች

ሁሉም ሰዎች በዚህ ፖሊሲ ስር የሚካተቱ ሰራተኞችን ጨምሮ ፤ ክትትል በማይደረግበት ሁኔታ ከልጆች ጋር ሊገናኙ የሚችሉ ሁሉ ከዲሲፒኤስ (DCPS) ተማሪዎች ጋር ከመስራታቸው በፊት ከዲሲፒኤስ ፍቃድ ቢሮ (DCPS Clearance Office) ፈቃድ ማግኘት አለባቸው።[3] የፍቃድ ማግኘቱ ሂደት የጣት አሻራ ላይ የተመረኮዘ የወንጀል ታሪክ ምርመራን ያካትታል። በተወሰነ ሁኔአታ ብቻ ሚስጥራዊ ሁኔታ ላይ ያሉ ወይም ከፍተኛ የሆነ የፌዴራል የደህንነት ክሊራንስ ካልሆነ በስተቀር ሌላ ምንም ዓይነት ክሊራንስ ተቀባይነት የለውም። የህይወት ታሪክ ምርመራው አሻራ ከተሰጠበት አንስቶ ለሁለት ዓመት ያገለግላል።[4]

[3] ሁሉም የኋላ የህይወት ታሪክ ጥናቶች በጣት አሻራ የሚሰሩ ሲሆን ብሄራዊ የወንጀል መረጃ ሴንተር (National Criminal Information Center) በ ሜየር እና በፌዴራል የምርመራ ቢሮ (Federal Bureau of Investigations (FBI)) ይደጋል።ዲሲ ህግ፤ ቁጥር 4-1501.05(ለ). የምርመራ ውጤቶቹ አሻራ ከተሰጠ ጊዜ አንስቶ ለሁለት አመታት ያገለግላሉ። ዲሲ ህግ፤ ቁጥር 4-1501.05(e)
[4] የበጎ ፈቃድ ሰራተኞች እና የዲሲፒኤስ (DCPS) ሰራተኞችም በምንም ዓይነት ሁኔታ ሲታሰሩ ወይም በወንጀል ሲከሰሱ ለአለቆቻቸው ማሳወቅ ይኖርባቸዋል። ይህ ማሳሰቢያ ከእስሩ ወይም የወንጀል መጥሪያ በደረሰ ከ 7 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ መደረግ አለበት። ይህንን ያለማድረግ በስነ-ስርዓት እርምጃ ያስቀጣል።(6-B DCMR ቁጥር 416.4)

3. የሰራተኛ ስነ-ምግባር መስፈርቶች[5]

ሰራተኞች በአላስፈላጊ ወሲባዊ ባህሪያት፤ የተማሪ ወሲባዊ ጥቃት እና የልጅ ጥቃት ሁኔታዎች ውስጥ ተሳታፊ ከመሆን በከፍተኛ ሁኔታ ይከለከላሉ። [6]

ሰራተኞች የሰራተኛው ውይም የተማሪው ዕድሜ ምንም ይሁን ምን ከተማሪዎች ጋር ጾታዊ ወይም የፍቅር ግንኙነት ውስጥ የመግባትም ሆነ የመገፋፋት ሁኔታ ውስጥ እንዳይሳተፉ በጥብቅ ይከለከላሉ። የተማሪው ወላጆች ሳያውቁ ወይም ሳይፈቅዱ ሰራተኞች ተማሪዎችን በግል መኪናቸው ውስጥ ከማስገባት፤ ወይም ከት/ቤት ውጪ እና ከትምህርት ሰዓት ውጪ ማግኘት በከፍተኛ ሁኔታ ይከለከላሉ። እነዚህ በከፍተኛ ህኔታ ክልክል የሆኑ ድርጊቶች ውስጥ የተሳተፈ ማንኛውም ሰራተኛ የስነ-ስርዓት እርምጃ ይወሰድበታል።

4. በሰራተኛ እና ተማሪዎች ከትምህርት ሰዓት ውጪ የሚደረግ ግንኙነት

When የዲሲፒኤስ (DCPS) ሰራተኞች ተማሪዎችን ከትምርት ሰዓት ውጪ ማግኘት ካለባቸው ግንኙነቱ በሚከተለው ሁኔታ ይፈጸማል።

(ሀ) በኢሜይል፤ የዲሲፒኤስ (DCPS) ሰራተኞች ከዲሲፒኤስ (DCPS) የተሰጣቸውን እማኢል አድራሻ መጠቀም ይጠበቅባቸዋል።

(ለ) በስልክ፤ የዲሲፒኤስ (DCPS) ሞባይል ስልክ የተሰጣቸው (DCPS) ሰራተኞች የተሰጣቸውን የሞባይል ስልክ ወይም ሌላ የዲሲፒኤስ (DCPS) ስልኮችን መጠቀም ይኖርባቸዋል። ሁሉም ሌሎች የዲሲፒኤስ (DCPS) ሰራተኞች በተቻለ መጠን የዲሲፒኤስን (DCPS) ቴሌፎን እንዲጠቀሙ ይገፋፋሉ።

(ሐ) በቴክስት፤ የዲሲፒኤስ (DCPS) ሞባይል ስልክ የተሰጣቸው (DCPS) ሰራተኞች የተሰጣቸውን የሞባይል ስልክ መጠቀም ይኖርባቸዋል።

ማንም ከዲሲፒኤስ (DCPS) ጋር የኮንትራት ውል የሚፈጽም አካል ሰራተኛ (በዚህ ክፍል "የዲሲፒኤስ ኮንትራት ተዋዋይዎች " ወይም ደግሞ ት/ቤቱ የስምምነት ውል ወይም የመግባቢያ ውል በማድረግ ት/ቤቱ አብሮ የሚሰራው አካል ተቀጣሪ (በዚህ ክፍል "አጋር") ከት/ቤቱ ዳይሬክተር ወይም ወላጅ የጽሁፍ ፈቃድ ሳያገኙ ከትምህርት ቤት ሰዓት ውጪ ተማሪን መገናኘት አይፈቀድላቸውም። የጽሁፍ ፈቃድ ከተሰጣቸው ግንኙነቱ በሚከተለው መልኩ መሆን ይኖርበታል፤

(ሀ) በኢሜይል፤ የዲሲፒኤስ (DCPS) የኮንትራት ተዋዋዮች ወይም አጋሮች ከዲሲፒኤስ (DCPS) የተሰጣቸውን እማኢል አድራሻ ወይም ደግሞ ኮንትራቱን ከተዋዋለው ህጋዊ አካል የተሰጣቸውን የኢሜይል አድራሻ መጠቀም ይጠበቅባቸዋል።

(ለ) በስልክ፤ የዲሲፒኤስ (DCPS) ሞባይል ስልክ የተሰጣቸው (DCPS) የኮንትራት ተዋዋዮች የተሰጣቸውን የሞባይል ስልክ ወይም ሌላ የዲሲፒኤስ (DCPS) ስልኮችን መጠቀም ይኖርባቸዋል። ሁሉም ሌሎች የዲሲፒኤስ (DCPS) የኮንትራት ተዋዋዮች በተቻለ መጠን የዲሲፒኤስን (DCPS) ቴሌፎን እንዲጠቀሙ ይገፋፋሉ።

---

[5] የዲሲፒኤስ የሰራተኛ መብቶች እና ሃላፊነቶች ፖሊሲ (DCPS Employee Rights and Responsibilities Policy) ይመልከቱ። በድረ-ገጽ : https://dcps.dc.gov/page/dcps-policies ይገኛል።

[6] በት/ቤት በጾታ ልዩነትን የሚከለክለውን፤የ 1972ቱን የተሻሻለውን የትምህርት ህግ ፤ ርዕስ IX (Education Amendments Act of 1972 ("Title IX")፤ እና በጾታ እና ጾታዊ ፍላጎት ላይ ተመርኩዞ የሚደረግ ልዩነትን የሚከለክለውን የ 1977ቱን ዲሲ ሰብዓዊ መብቶች ህግ ("D.C. Human Rights Act") ይመልከቱ።

(ሐ) በቴክስት፤ የዲሲፒኤስ (DCPS) ሞባይል ስልክ የተሰጣቸው (DCPS) የኮንትራት ተዋዋዮች የተሰጣቸውን የሞባይል ስልክ መጠቀም ይኖርባቸዋል።

ማንም የዲሲፒኤስ (DCPS) የበጎ ፈቃድ ሰራተኛ ከት/ቤቱ ዳይሬክተር ወይም ወላጅ የጽሁፍ ፈቃድ ሳያገኙ ከትምህርት ቤት ሰዓት ውጪ ተማሪን መገናኘት አይፈቀድላቸውም።

ሰራተኞች ግንኙነታቸውን በአሁን ሰዓት በዲሲፒኤስ (DCPS) ተመዝግበው ካሉ ወይም ከቀድሞ ተማሪዎች ጋር ብቻ (የተማሪው ዕድሜ ምንም ይሁን ምን) ማድረግ አለባቸው ። ሰራተኞች ከተማሪዎች ጋር የራሱን ወይም የራሷን የግል የመጠቀሚያ ስም ወይም ማህበረሰባዊ ሚዲያ ብቻ የሚገናኘው ተማሪው እንደሚከተሉት የሆነ እንደሆን ብቻ ነው፤

(ሀ) ዘመድ፤

(ለ) አንድ ዓይነት የሲቪክ፤ የማህበረሰብ መዝናኛ፤ የአትሌቲክ ወይም ሃይማኖት ድርጅት አባል ወይም ተሳታፊ ከሆነ፤ ወይም

(መ) በድንገተኛ ሁኔታ ምክንያት ግንኙነቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ። ይህ በሚያጋጥምበት ጊዜ ሰራተኛው ወዲያውኑ ለበላይ ተቆጣጣሪው ስለግንኙነቱ በተቻለ መጠን ወዲያውኑ ማሳወቅ ይኖርበታል።

የዲሲፒኤስ (DCPS) ሰራተኞች ለሙያዊ እና ለግል የመገናኛ ብዙሃን አጠቃቀም የበለጠ መረጃ ለማግኘት የዲሲፒኤስ (DCPS) የማህበረሰብ የመገናኛ ብዙሃን ፖሊሲን (Social Media Policy ) ማየት ይኖርባቸዋል። [7]

### (ለ) በሰራተኞች ለተፈጸመ የተማሪ ወሲባዊ ጥቃት ምላሽ መስጠት

5. ለዲሲፒኤስ (DCPS) ት/ቤት መሪዎች ሪፖርት የማድረግ መስፈርቶች

አግባብነት በሌለው ወሲባዊ ስነ-ምግባር፤ የተማሪ ወሲባዊ ጥቃት፤ እና በልጅ ጥቃት የተጠረጠሩ ሁሉም ክስተቶች ለMPD፤ CFSA እና ለ ሁሉን አቀፍ አማራጭ መፍትሄ ማዕከላዊ ቢሮ (Central Office Comprehensive Alternative Resolution & Equity (CARE) ቡድን[8] የህክምና እና የደህንነት ሁኔታዎ ከተፈሸሙ በኋላ ወዲያውኑ ሪፖርት መደረግ አለባቸው። የትምህርት ቤት መሪዎች፤

- 911 በመደወል የሜትሮፖሊታን ፖሊስ ክፍልን (Metropolitan Police Department (MPD) መገናኘት፤
- የህጻናት እና ቤተሰብ አገልግሎቶች አስተዳደርን (Child and Family Services Administration (CFSA)) በ (202) 671-SAFE(7233) በመደወል መገናኘት፤ እና
- የማእከላዊ ኬር ቢሮ ቡድንን (Central Office CARE Team) በ (202) 442-5405 በመደወል ወይም በ dcps.care@dc.gov ኢሜይል በመጻፍ መገናኘት ይኖርባቸዋል።

የት/ቤት መሪዎች በተጨማሪም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጨምሮ ሁሉንም የዲሲፒኤስ (DCPS) ክስተትን ሪፖርት የማድረግ መስፈርቶች (incident reporting requirements)[9] መከተል ይኖርባቸዋል፤

---

[7] የዲሲፒኤስ ማህበራዊ ሚዲያ ፖሊሲ (DCPS Social Media Policy) በ https://dcps.dc.gov/page/dcps-policies ድረ-ገጽ ይገኛል።
[8] የዲሲፒኤስ ኬር ቡድን (DCPS CARE Team) በማግለል ላይ ለሚቀርቡ አቤቱታዎች፤ ወሲባዊ ጥቃት፤ ቡሊንግ ወይም ተማሪን፤ ወላጅን ወይም ዲሲ የህዝብ ት/ቤት ውስጥ (DC Public School) የመጣን ጎብኚ አግባብነት በሌለው ሁኔታ መስተናገድን ወይም ለሚገጥሙ ችግሮች ሃላፊ ነው።
[9] በዲሲፒኤስ የተማሪ ደህንነት (DCPS Student Safety) ድረ-ገጽ፤ https://dcps.dc.gov/page/student-safety ላይ ይገኛል።

- ክስተቱን ሪፖርት ማድረጉ መጠናቀቁን እና መተላለፉን ለማረጋገጥ የት/ቤትዎን የደህንነት ሰራተኛ ወዲያውኑ መገናኘት[10]
- በክሪቲካል ኢንሲደንት ትራከር (Critical Incident Tracker)[11] የክስተቱን ሪፖርት ማስገባት፤
- ክስተቱ ማንኛውንም የዲሲፒኤስ (DCPS) ሰራተኛ ያካተተ ከሆነ  የሰው ሃይል አስተዳደር እና የሰራተኛ ግንኙነት (Labor Management and Employee Relations (LMER) በስልክ ቁጥር (202) 442-5374 ወይም በ dcps.lmer@dc.gov ማግኘት።

6. ለሁሉም ሌሎች ሰራተኞች ሪፖርት የማድረግ መስፈርቶች

ሁሉንም አስፈላጊ መስፈርቶች[12] ከማሟላት በተጨማሪ  ሰራተኞች ሁሉንም አግባብነት የሌለው ወሲባዊ ስነ-ምግባር፤ የተማሪ ወሲባዊ ጥቃት፤ እና በልጅ ጥቃት ለዳይሬክተሩ ወይም ለተወካዩ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው።

ሁሉም ከ ዲሲፒኤስ (DCPS) ውጪ የሆነ ሰራተኛ ሁሉንም አግባብነት የሌለው ወሲባዊ ስነ-ምግባር፤ የተማሪ ወሲባዊ ጥቃት፤ እና በልጅ ጥቃት ለዳይሬክተሩ ወይም ለተወካዩ እንዲሁም በትምህርት ቤት ላለ ለበጎ ፍቃድ ሰራተኞች፤ ለኮንትራክተሮች ወይም ለት/ቤት መርሃግብር አገልግሎት ሰጪዎች  ለተወከላ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው። ሁሉም የኮንትራት ተዋዋዮች እና የት/ቤት መርሃግብር አገልግሎት ሰጪዎች ሁሉንም ክስተቶች ኮንትራቱ ወይም የውል ስምምነቱ[13] ላይ ለተጠቀሰው ማዕከላዊ ቢሮ ሪፖርት ድረግ አለባቸው።

7. በሰራተኛ ስለተፈጸመ ዊሲባዊ ጥቃት ክስተት እና ምርመራውን በሚመለከት ለት/ቤቱ ማህበረሰብ ማሳወቅ

በሰራተኛ የተፈጸመ የተማሪ የወሲብ ጥቃት ሲቀርብ ዲሲፒኤስ (DCPS) የሰራተኞች የስነ-ምግባር ጉድለቶች ግንኙነቶችን ሂደት (Personnel Misconduct Allegations Communications Process) ፤ በዲሲፒኤስ የተማሪ ደህንነት ድረ-ገጽ ላይ https://dcps.dc.gov/page/student-safety የሚገኘውን ማለት ነው፤ ይጀምራል።

## ለ. የህዝብ ግንዛቤ እና የወላጅ ስልጠና

8. የህዝብ ግንዛቤ

የእያንዳንዱ የዲሲፒኤስ (DCPS) ት/ቤት ዳይሬክተር ይህ ፖሊሲ በት/ቤቱ ድረ-ገጽ ላይ መቀመጡን ያረጋግጣል። የእያንዳንዱ የዲሲፒኤስ (DCPS) ት/ቤት ዳይሬክተር ይህ ፖሊሲ ለሰራተኞች፤ ለወላጆች፤ እና ለእድሜ ተገቢ መሆኑን ባገናዘበ መልኩ ለተማሪዎች መድረሱን ያረጋግጣል። ት/ቤቶች ፖሊሲውን ለሰራተኞች እና ለወላጆች በህትመት ወይም በኤለክትሮኒክ ማቅረብ ይችላሉ። ፖሊሲውን በኤሌክትሮኒክ መልክ ለማቅረብ የመረጡ ት/ቤቶች የህትመት ቅጂ እንዴት ማግኘት እንደሚቻል መረጃ መስጠት አለባቸው።

---

[10] ክስተቱ በ6፡00 ፒኤም እና 8፡00 ኤኤም መካከል ወይም በዕረፍት ቀን የተፈጸመ ከሆነ አፋጣኝ መልስ ለማግኘት የዲሲፒኤስን ደህንነት ቡድንን የ24 ሰዓት መእከል (DCPS Security team's 24-hour Command Center) በስ.ቁ. (202) 576-6950 ያግኙ።

[11] ክሪቲካል ኢንሲደንት ትራከር (Critical Incident Tracker) የዲሲፒኤስ (DCPS) ሪፖርት ማድረጊያ (reporting database) ነው። በአሁን ሰዓት የሁለተኛ ት/ቤቶች እየተጠቀሙበት ሲሆን አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች በ2019 ክረምት ውቅት መጠቀም ይጀምራሉ።

[12] ዲሲ ኮድ (D.C. Code) § 4-1321.02)

[13] የትምህርት ቤት መርሃ-ግብር አቅራቢ የዲሲፒኤስ (DCPS) ተማሪዎችን ባህሪ፤ ደህንነት ወይም ጤንነት በሚመለከት ሪፖርት  ማድረግ አለበት። ወይም ማንኛውም የአገልግሎት አቅራቢ ሰራተኛ ከዲሲፒኢአስ ጋር ሲሰራ የተከሰተ ነገርን ለት/ቤት ዳይሬክተር፤ በት/ቤት ተጠሪ፤ በስምምነቱ ላይ ለተጠቀሰው የማዕከላዊ ቢሮ ተጠሪ፤  በኩል አስፈላጊውን ሪፖርት ማድረጊያ ቅጽ በመሙላት ማሳወቅ አለበት።

9. የወላጅ ስልጠና እና መረጃ

The የዲሲፒኤስ (DCPS) ማዕከላዊ ቢሮ የሚከተሉትንትምህርቶች ጨምሮ ስልጠና ማዘጋጀት እና ለወላጆች የልጅ በደልን፤ ወሲባዊ አላስፈላጊ ባህሪን፤ እና የተማሪ ወሲባዊ በደልን በሚመለከት መረጃ የመስጠት ሃላፊነት አለበት፤

(ሀ) ክሶችን ለሲኤፍሲኤ (CFSA)፤ ለኤምፒዲ (MPD) እና ለዲሲፒኤስ ማዕከላዊ ቢሮ ኬር ቡድን (DCPS Central Office CARE Team) ማቅረብ የሚቻልበትን መንገድ ጨምሮ አላስፈላጊ ወሲባዊ ባህሪያትን፤ የተማሪ ወሲባዊ ጥቃትን እና የልጅ ጥቃትን ማወቅ እና ሪፖርት ማድረግ፤
(ለ) አላስፈላጊ ወሲባዊ ባህሪያትን፤ የተማሪ ወሲባዊ ጥቃትን እና የልጅ ጥቃት ታሪኮችን ድጋፍ በሚሰጥ፤ ተገቢ በሆነ እና አስከፊነቱን ባገናዘበ መልኩ መቀበል፤
(ሐ) አላስፈላጊ ወሲባዊ ባህሪያትን፤ የተማሪ ወሲባዊ ጥቃትን እና የልጅ ጥቃትን ጠቋሚ የሆኑ ምልክቶችን እና ተጽእኖዎችን መከላከል፤
(መ) አላስፈላጊ ወሲባዊ ባህሪ፤ የተማሪ ወሲባዊ በደል እና የልጅ በደልን በሚመለከት ለመወያየት ጠቃሚና ለዕድሜ ተገቢ የሆነ ዘዴ መጠቀም፤ እና
(ሠ) አላስፈላጊ ወሲባዊ ባህሪ፤ የተማሪ ወሲባዊ በደል እና የልጅ በደልን ለመከላከልን ለመደገፍ በት/ቤት እና በማህበረሰብ የሚገኙ ግብዓቶች።

የት/ቤት ዳይረክተሮች በእያንዳንዱ የትምህርት ዓመት ቢያንስ አንድ የወላጅ ስልጠና በአካል መስጠት እና ሁሉንም የስልጠና ቁሳቁሶች እና ተዛማጅ መረጃዎች በት/ቤቱ ድረ-ገጽ ላይ ማስቀመጥ አለባቸው።

### (ሐ) በተማሪ ወሲባዊ በደል ለተጠቁ ተማሪዎች እና ቤተሰቦች ግብዓት፤ አገልግሎቶች እና መረጃ

ዲሲፒኤስ (DCPS) በወሲባዊ በደል ለተጠቁ ተማሪዎች የሚከተሉትን ማስረጃ ተኮር፤ እና ት/ቤት ተኮር የሆኑ የድጋፍ አማራጮችን ይሰጣል፤

- በትምህርት ቤት ለሚፈጸም አስከፊ ተሞክሮ የአስተሳሰብ እና ባህሪ ማስተካከል (Cognitive Behavioral Intervention for Trauma in Schools (CBITS)፤ ት/ቤት ተኮር፤ በቡድን እና በተናጠል በደሉ ከተፈጸመ በኋላ የሚኖርን ተሞክሮ (post-traumatic stress disorder (PTSD)፤ ድብርትን እና የባህሪ ችግርን ለመቀነስ እና የክፍል እና በት/ቤት መገኘትን እንዲያሻሽል ተደርጎ የተወጠነ የአቻ እና ወላጅ ድጋፍ እንዲሁም ከሁኔታ ጋር የመላመድ ክህሎት (coping skills)።
- ለድብርት እና ለአስከፊ በደሎች ለተጋለጡ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ባውንስ ባክ (Bounce Back) ማለትም ት/ቤት ላይ ያተኮረ ማስተካከያ (intervention)።
- ከተወሳሰበ የስሜት ቀውስ ጋር ተዛማጅ የሆኑ የማህበረሰብ እና የስሜት ዕክል ላለባቸው ጎልማሶች እራስን በመምራት ችግርን መቋቋም፤ የችግር አፈታት እና የግንኙነት ክህሎቶች ላይ ያተኮረ ለጎልማሶች ከፍተኛ ድብርትን ለመቋቋም የሚረዳ የተደራጀ የስነ-ልቦና ፈውስ (Structured Psychotherapy for Adolescents Responding to Chronic Stress (SPARCS))፤ (የተማሪ ደረጃ፤ መካከለኛ ትምህርት (MS ) እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት (HS))
- የጥቃት ወይም የአስከፊ ሃዘን ተሞክሮ ላላቸው ልጆች ከበደል በኋላ የሚከሰት የድብርት ምልክቶችን (PTSD) ለማስታገስ  የአስተሳሰብ ባህሪ እና የመተረክ ህክምና ዘዴዎችን በመጠቀም በት/ቤት ሃዘን እና ትካዜ (Grief and Trauma in School (GTI)። (የተማሪ ደረጃ፤ አንደኛ ደረጃ)።

የአካባቢ እና የብሄራዊ ግብዓቶችን፤ አገልግሎቶችን፤ እና መረጃዎችን ለያዙ ድረ-ገጾች እባክዎ አባሪ ለ ን ይመልከቱ።

**(መ) ሌሎች የተከለከሉ ድርጊቶች፤ የወደፊት የስራ ቅጥሮችን በመገምገም ወሲባዊ በደልን እንዳይከሰት መከልከል**

ከመደበኛው አስተዳደራዊ እና ገለሰባዊ ማህደርን የማስተላለፍ ሂደት በተጨማሪ ዲሲፒኤስ ወይም ሰራተኛው አንድ የትምህርት ቤት ሰራተኛ ለአቅመ አዳም ያልደረሱ ልጆች ላይ ህግን በመጣስ ወሲባዊ ጥቃት አድርሷል ብለው ካመኑ እና መፈጸሙንም ካወቁ ዲሲፒኤስ (DCPS) እና ሰራተኞች የትምህርት ሰራተኛን፤ የኮንትራት ሰራተኛን ወይም ወኪልን አዲስ ስራ እንዲያገኝ ከመደገፍ ይከለከላሉ[14] ፡፡ ማንኛውም በዚህ የተከለከለ ሁኔታ ውስጥ ተሳትፎ የተገኘ ሰራተኛ መባረርን ያካተተ የስነ-ሥርዓት እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

መንስኤ የሚሆነው መረጃ በትክክል ለ MPD፤ CFSA እና CARE ቡድን ከተነገረ እና ከዚህ በታች ያሉትን ሁኔታዎች ካካተተ ይህ ክልከላ ተፈጻሚ አይሆንም፤

(ሀ) ነገሩ በተገቢው ሁኔታ ከተዘጋ ወይም ከሰሹ ወይም ፖሊስ ነገሩን መርምሮ የት/ቤቱ ተቀጣሪ፤ የኮንትራት ተዋዋይ ወይም ወኪል በአላስፈላጊ ህግ ስለመጣሱ እና ለአቅመ አዳም ካልደረሱ ልጆች ጋር በተዛመደ ወሲባዊ ባህሪ ስለማሳየቱ በቂ መረጃ የሌለ መሆኑን ለት/ቤቱ ባለስልጣናት ካሳወቀ፤

(ለ) የት/ቤቱ ተቀጣሪ፤ የኮንትራት ሰራተኛ ወይም ወኪል ክሱ ከቀረበበት አላስፈላጊ ባህሪ ነጻ የሆነ እንደሆነ፤ ወይም

(መ) ጉዳዩ ወይም ምርመራው ክፍት ሆኖ በት/ቤት ተቀጣሪው፤ የኮንትራት ተዋዋዩ ወይም ወኪሉ ላይ ሁኔታው ለህግ አስፈጻሚዎች ሪፖርት ከተደረገ ጀምሮ በ4 ዓመታት ውስጥ ምንም ዓይነት ክስ ያልተመሰረተበት እንደሆነ፡፡

## V. ፖሊሲ ተግባራዊ የማድረግ መስፈርቶች

ሁሉም የዲሲፒኤስ (DCPS) ሰራተኞች በዚህ ፖሊሲ ላይ ለተጠቀሱ መስፈርቶች ታዛዥ መሆን ያስፈልጋቸዋል፡፡ የፖሊሲውን ተግባራዊነት ለመደገፍ ዳይሬክተሮች በየዓመቱ አስፈላጊ ነገሮችን እና የጊዜ ሁኔታዎችን ሰራተኛው እንዲያውቅ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ .

አስፈላጊው የሰራተኛ ስልጠና መጠናቀአ ቅና አለመጠናቀቅ በዲሲፒኤስ የሰራተኛ አገልግሎቶች ቢሮ (DCPS Office of Employee Services) ክትትል ይደረጋል፡፡ የእያንዳንዱ የ ዲሲፒኤስ (DCPS) ት/ቤት ዳሬክተር ከሰራተኛ አገልግሎቶች ቢሮ (DCPS Office of Employee Services) school ጋር በመቀናጀት ሁሉም የት/ቤት ሰራተኛ ይህንን መስፈርት ማሟላቱን የማረጋገጥ ሃላፊነት አለበት፡፡ የዚህ ፖሊሲ ተፈጻሚነት መደበኛ መረጃ መገምገምን፤ ነጮና መመዝገብን፤ አስፈላጎ ዶክመንቶችን መገምገምን እና (አስፈላጊ ሲሆንም) ቦታዎችን መጎብኘትን ባካተተ መልኩ በማዕከላዊ ቁጥጥር ሂደት ተግባራዊ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ ይህ ውጥን በጋራ በመሆን አለመታዘዝን የሚከላከል ተከታታይነት ያለው አሰራርን መገንበት እንደምንችል ያረጋግጣል፡፡

ዲሲፒኤስ (DCPS) እያንዳንዱን ተማሪ በፍትሃዊነት ፣ በከፍተኛ ጥራት ፣ ግልፅነት እና ተጠያቂነት ለማገልገል ቃል ገብቷል፡፡ ለማንኛውም ጥያቄ ወይም ይህንን መመሪያ ጥሰት በሚመለከት For any concerns about or violations of this directive, contact the የእንባ ጠባቂ ቢሮን (Office of the Ombudsman )(የቀድሞ ዋና ጽኑ ኦፊሰር (Chief Integrity Officer)) ድረ-ገጽ ላይ የሚገኘውን የማስተላለፊያ ፎርም (Online Referral Form[15] ) በመሙላት ወይም ወደ dcps.cio@dc.gov የኢሜይል መለእክት በመላክ ያግኙ፡፡

---

[14] ዲሲ ህግ፤ ቁጥር 38-951.02(a)(5)፤ እንዲሁም *see also* section 7926 of the Every Student Succeeds Act of 2015, approved ዲሴምበር 10 ቀን 2015 የጸደቀውን (129 Stat. 2120; 20 U.S.C. ቁጥር 7926)፤ የ 2015ቱን እያንዳንዱ ተማሪ ስኬታማ ይሆናል ህግ፤ ክፍል 7926 ይመልከቱ፡፡

[15] በድረ-ገጽ https://dcforms.dc.gov/webform/online-referral-form ላይ ይገኛል፡፡

አባሪ ሀ፡

በትምህርት ቤት ደኅንነት አዋጅ የጾታዊ በደል ትርጉም የተካተቱ አካባቢያዊ ሕጎች

የዲ.ሲ. ሕግ ቁ. 22-1834. የሕፃናት ወሲባዊ ንግድ

---

**(ሀ)** አንድ ግለሰብ ወይም ድርጅት የድርጊቱ ዓላማ ወሲባዊ ንግድ ተግባር ለመሳተፍ መሆኑንና የሰውየው እድሜ 18 ዓመት ያልደረሰ መሆኑን እያወቀ ወይም በግዴለሽነት ሆን ብሎ አንድን ሰው መመልመል፣ ማባበል፤ መጠለያ መስጠት፣ ማጓጓዝ፣ አቅርቦት ማድረግ፣ መያዝ፣ ወይም በማንኛውም መንገድ ድጋፍ መስጠት ሕገ ወጥ ተግባር ነው።

**(ለ)** በዚህ ክፍል ንዑስ ክፍል (ሀ) በሚመሠረት ክስ የተመለመለውን፣ በማባበል የተወሰደውን፣ መጠለያ የተሰጠውን፣ የተጓጓዘውን፣ አቅርቦት የተደረገለትን፣ የተያዘውን ወይም ድጋፍ የተደረገለትን ሰው ተከሳሹ በአግባቡ የማመዛዘን እድል ኖሮት ከሆነ የግለሰቡ እድሜ 18 ዓመት ያልሞላው መሆኑን ያውቅ እንደነበረ መንግሥት ማስረጃ የማቅረብ ኃላፊነት የለበትም።

የዲ.ሲ. ሕግ ቁ. 22-2704. አንድን ሕፃን ለዝሙት ተግባር ከመኖሪያ ቤቱ ወይም ቤቷ ስለመጥለፍ ወይም አባብሎ ስለመውሰድ፤ እንደዚህ ላለው ሕፃን መጠለያ ስለመስጠት

---

**(ሀ)** ለዝሙት ዓላማ፣ ማንኛውም ሰው የሚከተለውን ማድረግ ሕገወጥ ነው:

(1) እድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነን ሕፃን መገፋፋት፣ ማባበል ወይም ከመኖሪያ ቤቱ ወይም የተለመደ መኖሪያው ወይም ከሕፃኑ ወላጆች ወይም ሞግዚት እጅ በኃይል መጥለፍ፣ ወይም
(2) በዚህ ሁኔታ የተገፋፋውን፣ የተባበለውን ወይም ከመኖሪያ ቤቱ ወይም የተለመደ መኖሪያው ወይም ከሕፃኑ ወላጆች ወይም ሞግዚት እጅ በኃይል የተጠለፈው ሕፃን መደበቅ ወይም ለሕፃኑ መጠለያ መስጠት።

**(ለ)** የዚህን ክፍል ንዑስ ክፍል (ሀ)ን የተላለፈ ሰው የከባድ ወንጀል ጥፋተኛ እነደሆነ ይቆጠራል፣ በወንጀሉ ጥፋተኛ ሆኖ ከተወሰነም ከ20 ዓመት ባልበለጠ እሥራት ወይም በቁጥር 22-3571.01 ከተመለከተው በማይበልጥ የገንዘብ መጠን፣ ወይም በሁለቱም ይቀጣል።

**ከዲ.ሲ. ደንብ ርእስ 22 (የወንጀል ድርጊቶችና ቅጣቶች) ምዕራፍ 30 (ወሲባዊ በደል) የተውጣጡ**

ቁጥር. 22-3008. መጀመሪያ ደረጃ የሕፃናት ወሲባዊ በደል

---

በእድሜ ከሕፃኑ ቢያንስ በ4 ዓመት የሚበልጥ ማንኛውም ከሕፃኑ ወይም ከሕፃኗ ጋር የግብረ-ሥጋ ተግባር የፈጸመ ወይም ሕፃኑ ወይም ሕፃኗ የግብረ ሥጋ ተግባር እንዲፈጽም ያደረገ ሰው ለማንኛውም ዓመታት ወይም እድሜ ልክ ሊታሰር፣ እንዲሁም በቁጥር 22-3571.01 ከተመለከተው በማይበልጥ የገንዘብ መጠን ሊቀጣ ይችላል። ይሁን እንጂ ፍርድ ቤቱ በቁጥር 22-3020 ወይም 24-403.01(ለ-2) ተመስረቶ ከ30 ዓመት የሚበልጥ እስራት ሊወስን ይችላል። በቁጥር 24-403.01(ለ)(7) የተሰጠውን የመልቀቅ ሥልጣን በተመለከተ በዚህ ክፍል የተገለጸው ወንጀል መደብ ሀ ከባድ ወንጀል ነው።

ቁጥር 22-3009. ሁለተኛ ደረጃ የሕፃናት ወሲባዊ በደል

---

በእድሜ ከሕፃኑ ቢያንስ በ4 ዓመት የሚበልጥ ማንኛውም ሰው ከሕፃኑ ጋር የግብረ ሥጋ ተግባር የፈጸመ ወይም ሕፃኑ የግብረ ሥጋ ተግባር እንዲፈጽም ያደረገ ሰው ከ10 ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ይታሠራል። በተጨማሪም በቁጥር 22-3571.01 ከተመለከተው በማይበልጥ የገንዘብ መጠን ሊቀጣ ይችላል።

ቁጥር 22-3009.01. አካለ መጠን ባልደረሱ ሰዎች ላይ ስለሚፈጸም መጀመሪያ ደረጃ ወሲባዊ በደል

እድሜው 18 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ማንኛውም ሰው አካለ መጠን ካልደረሰ ልጅ ጋር ትርጉም ያለው ዝምድና ኖሮት ከልጁ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ቢፈጽም፣ ወይም አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዲፈጽም ቢያደርግ ከ15 ዓመት ባልበለጠ እስራት ይቀጣል። በተጨማሪ በቁጥር 22-3571.01 ከተመለከተው በማይበልጥ የገንዘብ መጠን፣ ወይም በሁለቱም ሊቀጣ ይችላል።

ቁጥር 22-3009.02. አካለ መጠን ባልደረሱ ልጆች ላይ ስለ ሚፈጸም ሁለተኛ ደረጃ ወሲባዊ በደል

እድሜው 18 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ማንኛውም ሰው አካለ መጠን ካልደረሰው ልጅ ጋር ትርጉም ያለው ዝምድና ኖሮት ከልጁ ጋር የግብረ ሥጋ ተግባር የመሰለ ንክኪ ቢፈጽም ወይም አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ የግብረ ሥጋ ተግባር የመሰለ ንክኪ እንዲፈጽም ቢያደርግ ከ7½ ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ እስራት ይቀጣል። በተጨማሪ በቁጥር 22-3571.01 ከተመለከተው በማይበልጥ የገንዘብ መጠን፣ ወይም በሁለቱም ሊቀጣ ይችላል።

ቁጥር 22-3009.03. በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተማሪዎች ላይ ስለሚፈጸም መጀመሪያ ደረጃ ወሲባዊ በደል

ማንኛውም አስተማሪ፣ አማካሪ፣ ርእሰ መምህር፣ አሠልጣኝ ወይም በአንድ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ሥልጣን ያለው ሌላ ሰው እድሜው ከ20 ዓመት በታች ከሆነ በዚያው ትምህርት ቤት ወይም የትምህርት ቤት ሥርዓት ውስጥ ከሚማር ተማሪ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ቢፈጽም ወይም የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዲፈጽም ቢያደርግ ከ10 ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ በእስራት ይቀጣል። በተጨማሪ በቁጥር 22-3571.01 ከተመለከተው በማይበልጥ የገንዘብ መጠን፣ ወይም በሁለቱም ይቀጣል።

ቁጥር 22-3009.04. በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ተማሪዎች ላይ ስለሚፈጸም ሁለተኛ ደረጃ ወሲባዊ በደል

ማንኛውም አስተማሪ፣ አማካሪ፣ ርእሰ መምህር፣ አሠልጣኝ ወይም በአንድ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ሥልጣን ያለው ሌላ ሰው እድሜው ከ20 ዓመት በታች ከሆነ በዚያው ትምህርት ቤት ወይም የትምህርት ቤት ሥርዓት ውስጥ ከሚማር ተማሪ ጋር የግብረ ሥጋ የመሰለ ባሕርይ ቢፈጽም ወይም የግብረ ሥጋ የመሰለ ባሕርይ እንዲፈጽም ቢያደርግ ከ5 ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ በእስራት ይቀጣል። በተጨማሪ በቁጥር 22-3571.01 ከተመለከተው በማይበልጥ የገንዘብ መጠን፣ ወይም በሁለቱም ይቀጣል።

ቁጥር 22-3010. ሕፃናትን ወይም አካለ መጠን ያልደረሱ ሰዎችን ስለማባበል

**(U)** በእድሜ ከሕፃኑ ቢያንስ በ4 ዓመት የሚበልጥ ወይም አካለ መጠን ካልደረሰው ሰው ጋር ትርጉም ያለው ዝምድና ያለው፣ (1) ከቁጥር 22-3002 እስከ 22-3006 እና ከ22-2008 እስከ 22-3009.02 የተመለከቱትን ማናቸውንም ወንጀል ለመፈጸም ሕፃኑን

ወይም አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ ወደ ማናቸውም ቦታ የወሰደ፣ (2) ሕፃኑ ወይም አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ወይም የግብረ ሥጋ ተግባር የመሰለ ንክኪ እንዲፈጽም የገፋፋ፣ ያባበለ፣ ያጓጓ፣ ያሳመነ ወይም ያበረታታ ወይም ለመገፋፋት፣ ለማባበል፣ ለማጓጓት፣ ለማሳመን ወይም ለመገፋፋት የሞከረ ማንኛውም ሰው ከ5 ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ ይታሰራል ወይም በቁጥር 22-3571.01 ከተመለከተው በማይበልጥ የገንዘብ መጠን፣ ወይም በሁለቱም ሊቀጣ ይችላል።

**(ለ)** ማንኛውም ሰው፣ ራሱን ከሚወክል ወይም ራሷን ከምትወክል ሕፃን በእድሜ ቢያንስ 4 ዓመት የሚበልጥ፣ የሚከተሉትን ቢሞክር (1) ራሱን የሚወክል ወይም ራሷን የምትወክል ሕፃን የግብረ ሥጋ ግንኙነት ወይም የግብረ ሥጋ ተግባር የመሰለ ንክኪ እንዲፈጽም ወይም እንድትፈጽም የገፋፋ፣ ያባበለ፣ ያጓጓ፣ ያሳመነ ወይም ያበረታታ ሰው ወይም (2) የግብረ ሥጋ ግንኙነት ወይም የግብረ ሥጋ ተግባር የመሰለ ንክኪ ለመፈጸም ማናቸውንም ራሱን የሚወክል ወይም ራሷን የምትወክል ሕፃን ወደ ማናቸውም ቦታ እንዲሄድ ወይም እንድትሄድ ያባበለ፣ ያጓጓ፣ ያሳመነ ወይም ያበረታታ ሰው ከ5 ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ ይታሰራል ወይም በቁጥር 22-3571.01 ከተመለከተው በማይበልጥ የገንዘብ መጠን ወይም በሁለቱም ሊቀጣ ይችላል።

**(ሐ)** የማጓጓቱ ተግባር ከግብረ ሥጋ ግንኙነቱ ወይም የግብረ ሥጋ ተግባር ከመሰለው ንክኪ ጋር በተቀራራቢ ጊዜ የተፈጸመ ከሆነ ማንኛውም ሰው አንድን ሕፃን ወይም አካለ መጠን ያልደረሰ ሰው የግብረ ሥጋ ግንኙነት ወይም የግብረ ሥጋ ተግባር የመሰለ ንክኪ እንዲፈጽም በማጓጓቱ ምክንያት በዚህ ክፍል ንዑስ ክፍል (ሀ)(2) መሠረት ተከታታይ ቅጣት አይጣልበትም።

ቁጥር 22-3010.01. ከባድ ያልሆነ የሕፃናት ወይም አካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች ወሲባዊ በደል

---

**(ሀ)** ማንኛውም እድሜው 18 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ እና ከሕፃኑ በእድሜ ከ4 ዓመት በላይ የሆነ ወይም እድሜው 18 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ሆኖ አካለ መጠን ካልደረሰው ሰው ጋር ትርጉም ያለው ዝምድና ያለው ሰው በሕፃኑ ወይም አካለ መጠን ባልደረሰው ልጅ ላይ ለግብረ ሥጋ የማነሳሳት ባሕርይ ፈጽሞ ከሆነ ከ180 ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ይታሰራል፣ ወይም በቁጥር 22-3571.01 ከተመለከተው በማይበልጥ የገንዘብ መጠን፣ ወይም በሁለቱም ሊቀጣ ይችላል።

**(ለ)** ለዚህ ክፍል አፈጻጸም ሲባል "ወሲባዊ ቀስቃሽ ባሕርይ" ማለት የማናቸውንም ሰው የወሲብ ፍላጎት ለመቀስቀስ ወይም ወሲባዊ እርካታን ለማግኘት በማለም ከሚከተሉት መካከል ማናቸውንም ተግባር መፈጸም ማለት ነው፦

**(1)** የሕፃኑን ወይም አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ ከልብሱ ውስጥ ገብቶ መንካት፤

**(2)** በሕፃኑ ወይም አካለ መጠን ባልደረሰው ልጅ ብልት፣ ፊንጢጣ፣ ጡት ወይም መቀመጫ አካል አካባቢ በልብስ ላይም ሆነ ውስጥ መንካት፤

**(3)** በሕፃኑ ወይም አካለ መጠን ባልደረሰው ልጅ አፍ ውስጥ ምላስን ማስገባት፤ ወይም

**(4)** የራስን ወይም የሌላ ሦስተኛ ሰው ብልት መንካት።

ቁጥር 22-3010.02. በእውን ካለ ወይም ምናባዊ ሕፃን ጋር ወሲባዊ ንክኪ ለመፈጸም ማመቻቸት

---

**(1)** እድሜው ከግለሰቡ ቢያንስ በ4 ዓመት ከሚያንስ ሕፃን ወይም ሕፃን ተብሎ ከሚታሰብ (በእውን ያለም ሆነ ምናባዊ) ጋር የወሲባዊ ተግባር ወይም ወሲባዊ ተግባር የመሰለ ንክኪ ለመፈጸም ዝግጅት ማድረግ ወይም እድሜው ከሰውየው ቢያንስ በ4 ዓመት ከሚያንስ ሕፃን ወይም ሕፃን ተብሎ ከሚታሰብ ሰው (በእውን ያለም ሆነ ምናባዊ) ጋር የወሲባዊ ተግባር ወይም የወሲባዊ ተግባር የመሰለ ንክኪ ለመፈጸም ለሌላ ሰው ማመቻቸት ሕገወጥ ተግባር ነው። ለዚህ ክፍል አፈጻጸም ሲባል ምናባዊ ግለሰብ ጋር ወሲባዊ ግንኙነት ለመፈጸም ወይም ወሲባዊ ተግባር የመሰለ ንክኪ ለመፈጸም ማመቻቸት ሕገ ወጥ የሚሆነው ድርጊቱ በሕግ አስከባሪ መኮንን ወይም ከሕግ አስከባሪ መኮንን ጋር ከሆነ ብቻ ነው።

**(ለ)** የዚህን ክፍል ንዑስ ክፍል (ሀ) የተላለፈ ሰው ከ5 ዓመት ለማይበልጥ ጊዜ ይታሰራል፣ በቁጥር 22-3571.01 ከተመለከተው በማይበልጥ የገንዘብ መጠን፣ ወይም በሁለቱም ይቀጣል።

ቁጥር 22-3011. የሕፃናት እና አካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች ላይ ወሲባዊ በደል ለማድረስ የሚቀርቡ መከላከያዎች

---

**(ሀ)** ከቁጥር 22-3008 እስከ 22-3010.01 ባሉት ሥር ብቻውን ወይም በቁጥር 22-3018 ወይም 22-403 ሥር ካሉት ጋር በጥምራ ለተመሰረተ ክስ የእድሜ ስህተትም ሆነ ፈቃደኝነት እንደ መከላከያ ሆኖ መቅረብ አይችልም፡፡

**(ለ)** ወንጀሉ በተፈጸመበት ጊዜ በሕፃኑ ወይም አካለ መጠን ባልደረሰው ልጅና በተከሳሹ መካከል የጋብቻ ወይም አብሮ የመኖር ግንኙነት መኖሩ እንደ መከላከያ መቅረብ ይችላል፡፡ ከቁጥር 22-3008 እስከ 22-3010.01 ባሉት ሥር ብቻውን ወይም በቁጥር 22-3018 ወይም 22-403 ሥር ካሉት ጋር በጥምራ ለተመሰረተ ክስ ተከሳሹንና ሕፃኑን ወይም አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ ብቻ በተመለከተ ተከሳሹ በማስረጃው ክብደት ማስረዳት ይኖርበታል፡፡

ቁጥር 22-3012. የአእምሮ ጤና ማስረጃ መስፈርት

---

ከቁጥር 22-3008 እስከ 22-3010.01 ባሉት ሥር ብቻውን ወይም በቁጥር 22-3018 ወይም 22-403 ሥር ካሉት ጋር በጥምራ ለተመሰረተ ክስ ተከሳሹ የሕፃኑን እድሜ ወይም በእሱ/በእሷና በሕፃኑ መካከል የነበረውን የእድሜ ልዩነት ያውቅ እንደነበረ መንግሥት ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ የለበትም፡፡

[. . .]

ቁጥር 22–3018. ወሲባዊ ጥቃት ለማድረስ መሞከር

---

በዚህ ንኡስ አንቀጽ ስር የተመለከተውን ለመጣስ የሞከረ ማንኛውም ሰው ከ15 ያልበለጠ እስር ሲሆን ለጥፋቱ የተቀመጠው ከፍተኛው እስር ህይወት ሙሉ ነው፤ ወይም ለጥፋቱ የተመለከተውን እስር ½ኛ በላይ እና ከከፍተኛው ቅጣት ከ1/2ኛ ያልበለጠ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል፡፡

ቁጥር 22–3019. ለባለትዳሮች ወይም ለቤት አጋሮች ክስ ከመመስረት ነፃ የሆነ መከላከያ የለም""

---

በዚህ ንዑስ ክፍል ማንም ቢሆን በጋብቻ፤ በዝምድና ወይም ከተበዳይ ጋር ባለ ቅርርብ ምክንያት ከመከሰስ አያመልጥም፤ የጋብቻ ውይም በዝምድና የተሳሰሩ በግልጽ በተሰጠበት በዚህ ንዑስ ስር በግልጽ እንደተመለከተው ክስ እንደ ክስ ማረጋገጫ ሆኖ ሊቆጠር ይችላል

ቁጥር 22–3020. አባባሽ ሁኔታዎች

---

**(ሀ)** በዚህ ንዑስ ክፍል ስር ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ማንኛውም ሰው እስከ 1 ½ ጊዜ የሚሆን ሊቀጣ የሚችል ሲሆን ፣ የሚከተሉት ማንኛውም ዓይነት አባባሽ ሁኔታዎች ካሉ የመለቀቅ ሁኔታ ሳይኖር እስከ 30 ዓመት ወይም እድሜ ልክ የሚደርስ እስራትም ሊቀበል ይችላል፤

**(1)** ተበዳዩ ጥቃቱ በሚፈጸምበት ወቅት ከ12 ዓመት በታች ከሆነ፤

**(2)** ተበዳዩ ጥቃቱ በሚፈጸምበት ወቅት ከ18 ዓመት በታች ከሆነ እና በዳዩ ከተበዳዩ ጋር ጉልህ የሆነ ግንኙነት ካለው፤

**(3)** ተበዳዩ በበደሉ ምክንያት ከፍተኛ የአካል ጉዳት የደረሰበት እንደሆነ፤

**(4)** ተከሳሹ ከ1 ወም ከዚያ በላይ በሆኑ ተሳታፊዎች ታግዞ ከሆነ፤

**(5)** ተከሳሹ በ2 ወይም ከዚያ በላይ ተበዳዮች ላይ በደል ማድረሱ፤ በዚያውም ሆነ በሌላ የፍርድ ሂደት፤ በዲሲ፤ በማንኛውም ክልል፤ ወይም አሜሪካ ግዛት ፍርድ ቤት ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ከሆነ፤ ወይም

**(6)** ተከሳሹ ሽጉጥ ወይም ሌላ የጦር መሳሪያ ወይም ሌላ አደገኛ መሳሪያ ታጥቆ ከሆነ ወይም አዘጋጅቶ ከሆነ (ወይም ያለም መሆኑን አስመስሎ) ከሆነ።

**(ለ)** ተሳታፊዎችሁ  በዚህ ክፍል ንዑስ አንቀጽ (ሀ) (4) ላይ ለተመለከተው ለተጨማሪ ቅጣት (ወይም በተሻሻለ ቅጣት) ጥፋተኛ ሆነው መገኘታቸው አስፈላጊ አይደለም ።

**(ሐ)** የፍርድ ሂደት ከመጠየቁ በፊት ወይም የይግባኝ ጥያቄው ከመግባቱ በፊት በዚህ ንዑስ ባለ ሥልጣኑ ጥፋተኛ ሆኖ የተከሰሰ ማንኛውም ሰው በዚህ ክፍል ንዑስ አንቀጽ (ሀ) ላይ በተመለከቱት አስከፊ ሁኔታዎች ምክንያት ለተጨማሪ የቅጣት (ወይም የተሻሻለ ቅጣት) አይዳረግም ። የአሜሪካ  ጠበቃ ወይም የኮርፖሬሽኑ አማካሪ ፣ እንደሁኔታው ፣ ለፍርድ ቤቱ ዋና ጸሐፊ መረጃ ያስረክባል ፣ እናም በእነዚያ ላይ የግለሰቦችን ምክንያቶች በጽሁፍ በመግለጽ ግለሰቡ ወይም ምክር ላይ ግልባጭ ይሰጣል ።

## አባሪ ለ፤
## በተማሪ ወሲባዊ በደል ለተጠቁ ተማሪዎች እና ቤተሰቦች አካባቢያዊና ብሄራዊ ግብዓቶች፤ አገልግሎቶች እና መረጃዎች

### አካባቢያዊ ግብዓቶች፤ አገልግሎቶች እና መረጃ

- ዲሲ የባህሪ እና ጤና አገልግሎት ማግኛ መስመር (DC Department of Behavior Health Access HelpLine)
  1-888-7WE-HELP (793-4357)

- ዲሲ የደፈር ጥቃት ማዕከል (DC Rape Crisis Center)
  http://dcrcc.org/
  202-333-RAPE (7273)

- የዲሲ ከጥቃት የማገገም ግንኙነት (Network for Victim Recovery of DC)
  https://www.nvrdc.org/
  202-742-1727

- ሴፍ ሾርስ ዲሲ የህጻናት የቆመ ማዕከል (Safe Shores DC Children's Advocacy Center)
  https://www.safeshores.org
  (202) 645-3200

### ብሄራዊ ግብዓቶች፤ አገልግሎቶች እና መረጃዎች

- አር ኤ አይ ኤን ኤን (RAINN) (Rape, Abuse & Incest National Network)
  https://www.rainn.org
  800-656-HOPE (4673)

- ብሄራዊ ወሲባዊ በደል ግብዓት ማዕከል (National Sexual Violence Resource Center)፤
  https://www.nsvrc.org,
  - ጓደኞች እና ቤተሰብ አብዓቶች (Friends & Family Resources)፤
    https://www.nsvrc.org/friends-family

- ስቶፕ ናው (Stop It Now)!
  https://www.stopitnow.org,